www.ethiopianorthodox.org

# እኔም ወጣት ነበርኩ



አቶ ዓለመ ሥላሴ ጕላ የታላቁ የአለቃ ጕላ መታፈሪያ ልጅ ናቸው። በዛው ላይ ከታወቁት ሊቅ ከየኔታ ወልደ ሥላሴና ከዝነኛው ባለቅኔ አለቃ ለማ የሐዲሳትና የቅኔ ዕውቀ ታቸውን አበልጽገዋል። በአጭሩ አቶ ዓለመ ሥላሴ ጕላ በቅኔ ባሕር ተወል ደው በቅኔ ባሕር እየዋኙ ነው ያደጉት ማለት ይቻላል።

አቶ ዓለመሥላሴ የ፹፮ ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ናቸው። እንደዛም ሆነው መኪና ያሽከረክራሉ ያለመነ ጽር ያነባሉ። ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ የትምህርት ሚኒስቴርን «ሀ» ብለው ካቋቋሙትና በአዲስ መልክ አደራ ጅተው አሁን ላለበት ደረጃ ካደረሱት ጥቂት ሰዎች አንዱ የሆኑት አቶ ዓለመ ሥላሴ ከ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ጀምሮ ጡረታ እስከወጡበት ፲፱፻፷፰ ድረስ ከጸሐ ፊነት እስከ ዋና ዴሬክተርነት ባሉት የተለያዩ የሥልጣን እርከኖች ሠርተዋል።

በቀድሞው የተፈሪ መኮንን ት/ቤት ገብተው ዘመናዊ ትምህር ታቸውን ከመከታተላቸው በፊት ቅኔ፣ ሐዲሳትን ከብሉይ አራቱ ክፍለ ነገሥታትን ውዳሴ ማርያምንና ዜማን በሚገባ አጠናቀዋል። ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ባላነሰ እንዳሻቸው አቀላጥ ፈው ከሚያዙት ግዕዝ ሌላ ኢጣሊ ያንኛ፣ ሶማሊኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋ ዎችን ይችላሉ።

የዛሬው የ«እኔም ወጣት ነበርኩ» አምድ እንግዳችን አቶ ዓለመ ሥላሴ ጕላ ሰፊ ዕውቀት፣ ተዝቆ የማያልቅ የሥራ ተመክሮ ያላቸው አዛውንት ናቸው። እንደዛም ሆኖ «ቁጥብነት»

## ዓለመ ሥላሴ ጕላ

### ባለቅኔው የትምህርት ዓምድ

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ያሸንፋቸዋል። በቀጠሮየ መሠረት መቅረጸ ድምጼንና መቅረጸ ምስሌን ይዤ ቤታቸው ስደርስ በታላቅ ትህት ናና አክብሮት ከተቀበሉኝ በኋላ ያቀረ ቡልኝ የመጀመሪያ ጥያቄ «ስለ ሕይወት ታሪኬ ብዙ አይጠይቁኝ የሕይወት ታሪኬ እንዲጻፍ አልፈ ልግም፣ ይህን ሠራሁ ይህን አደረግሁ ማለትን አልወድም» ነበር ያሉኝ።

ቃለመጠይቄን ጨርሼ፣ የመጣሁ በትን ጉዳይ ፈጽሜ፣ በሥነ ጥበብ ውጤቶች (በሥዕሎች ፎቶግራፎችና ልዩ ልዩ የእደ ጥበባት ሥራዎች) ያሸበረቀችውን ሳሎናቸውን ለቅቄ ልወጣ ስል ወደ ቤት ስገባ የነገሩኝን ደግመው አስታወሱኝ። በአደራ መልክ። «...እኔ በተፈጥሮየ ልታይ ልታይ ማለትን አልፈልግም ይህንን ሲጽፉ በተቻለዎት መጠን ቀነስ አድርገው ይጻፉት...አደራዎትን» ብለው አሰናበቱኝ። አባባላቸው የሊቃውንት አበው አባባል በመሆኑ በጣም ደስ አለኝ። እኔም ትህትና



የተላበሰውን የአደራቸው ቃል ለማክበር ስል ካካፈሉኝ ቁና ሙሉ ቁም ነገር አንዷን ጭልፋ ጨልፌ ለማቅረብ ወሰንኩ፤ መልካም ንባብ።

**ፈለገ ጥበብ** – የትና መቼ ተወለዱ?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ሃራምባ ቅዱስ ሚካኤል በተለይ በለስ ተብላ በምትጠራው ሥፍራ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፮ ዓ.ም ተወለድኩ። ደብሩ ጥንታዊ ነው። አብዮና ስብስቴ የተቀበሩበት ነው፣ የተቋቋመው በ፲፯፻፹፰ ዓ.ም ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ወደራስዎ እንመለስና ስለ ልጅነት ጊዜዎ ትንሽ ቢያወጉኝ?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – እዛ ከተወ ለድኩበት ሃራምባ ነው ያደግሁት፣ የተማርኩትም፣ ቅኔም የተቀኘሁት እዛው ነው። መጽሐፍ ለመማር ብቻ ነው አንኮበር የሄድኩት። እዛም ከሐዲስ ተክሌ ሐዲሳትን አነበብኩ ከኔታ ወልደ ሥላሴም ሐዲሳትን፣ ከብሉያትም አራቱ ክፍለ ነገሥት አነበብኩ፣ ከዛም አዲስ አለም ከየኔታ ቴዎድሮስ ውዳሴ ማርያም ዜማ ተማ ርኩ። ሐረር ድረስ በመሄድ ከታወቁ አለቃ ለማ ዘንድ ለሁለት ዓመታት ሐዲሳትን አንብቤአለሁ።

**ፈለገ ጥበብ** – አባትዎ የታወቁ የቅኔ ሊቅ እንደ ነበሩ ይታወቃል፤ ከሳቸው ዘንድ ቅኔ አልተማሩም ማለት ነው?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – አልተማርኩም፣ ሥራ ነበራቸው አለቃ ናቸው፣ ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፣ በዛው ላይ አዲስ ዓለም ትክለኛ ናቸው ቁጭ አይሉም፣ አንዳንዴ ታድያ አባቴ ፊት ስቀኝ «ቃናዋ ደስ ትላለች፣ ትጣፍጣለች እንጂ ቀላል ናት» ይሉኝ ነበር።

**ፈለገ ጥበብ** – በዚህ ዓይነት የቆሎ ተማሪ ሆነው አያውቁም ማለት ነው?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – በጭራሽ አግኝቶኝም አያውቅ፣ አዲስ ዓለምም ቢሆን የአባቴም የአያቴም ቤት ስለ ነበር እዛ ቁጭ ብየ ነው የተማርኩት።

**ፈለገ ጥበብ** .– ዘመናዊ ትምህርት እስከ ስንተኛ ተምረዋል?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – እስከ ሦስተኛ እንደዚህ ነው የተማርኩት፣ በኋላ አባቴ ካቶሊክ ትሆናለህ ብለው አስወጡኝና ሐረር ሄድኩኝ በዛን ጊዜ ትያትርም እሠራ ነበር በዚህም ሽልማት አግኝቼአለሁ፣ ዘፈንም ግጥምም እችል ነበር።

**ፈለገ ጥበብ** – ከዛ በኋላ ትምህርትዎን አልቀጠሉም?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – ፈልጌ ነበር ነገር ግን ኢጣሊያን ሀገራችንን ወሮ እንደ ገባ አርባ የምንሆን ተማሪዎች ከት/ቤት አፍሶ ወደ ሞቃድሾ ወሰደን፣ እዛ ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል በግዞት ተቀመጥኩኝ።

**ፈለገ ጥበብ** – በሞቃዲሾ ስላሳለፉት የግዞት ሕይወት ሰፋ አድርገው ቢነግሩኝ?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – እሥረኞች አልነበርንም፤ የፖለቲካ ግዞተኞች ነን፣ ኮንፊናቲ ፖለቲቺ ይባላል፤ ቀን ለ፲፪ ሰዓት ነፃ ነን፤ የትም መሄድ እንችላለን ሥራ መሥራትም ይቻላል። ማታ ፲፪ ሰዓት ላይ ግን መገኘት ግድ ነው። ምግቡም የሚበቃ ነው፤ ሕክምናም በመጠኑ አለ። ልብስ ግን አይሰጠንም፣ ከቤተሰብ ገንዘብ ይላክልን ነበር ለእኔም አባቴ ይልኩልኝ ነበር። ከመካከላችን የተፈረደባቸው እስረኞችም ነበሩ። የአሰቦትና ደብረ ሊባኖስ ገዳማት መነኮሳትም እንዳሉ ታፍሰው ተወስደው ነበር። ለሞቱት ፍትሐት ያደርጉ ነበር። ያለ ማቋረጥ ምሕላና ጸሎት ያደርጉ ነበር።

**ፈለገ ጥበብ** – በመጨረሻ እንዴት ወደ ሀገርዎ ተመለሱ?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – የሁለተኛ ዓለም ጦርነት ሲጀመር አንድ ኮሌኔል እስረኞችን ሰበሰበንና (ከሦስት ሺህ እንበልጣለን) «አሁን የኢጣሊያ መንግሥት ከባድ ሥራ አለበት እናንተ ወደ ሀገራችሁ ትመለሳላችሁ ጠባያችሁ ጥሩ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ሀገራችሁ ስትገቡ እንደ አሁኑ መታሰር የለም፣ ጠባያችሁ ካላማረ ግን ትመታላችሁ» አለንና ተራ በተራ ላከን። እዚህ መጣን። እዚህም የጣልያን መንግሥት ነው ያለው አፌች ፖለቲኮ የሚባል አለ፣ ማታ ነበር የደረስነው፣ በማግስቱ ሄደን ነፃ ናቸው የሚል ወረቀት ተሰጠን። መነኮሳቱ ግን ከኛ ቀደም ብለው ነበር የተመለሱት።

በኋላ እኔ፣ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ደነቀ/ሰሸናፊ የሚባል ሌላም ጓደኛ ነበረን ሀገራችን እንገባለን ብለን ስንብት (ፈቃድ) ጠየቅን። የለም እዚሁ ሥራ እንሰጣችኋለን አሉንና እኔን ከፖለቲካው ምክትል ዲሬክተሩ ጋር (እሱ በመጠኑ ግዕዝ ያውቅ ስለነበር እኔን በመምረጡ) ተክለፃድቅን አመያ (ወሊሶ አካባቢ) ሰደዱት፣ ደነቀን ደግሞ ፍቼ በመውሰድ ሦስታችንንም ለያዩን።

**ፈለገ ጥበብ** – ከነፃነት በኋላስ?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – ከነፃነት በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሠርቻለሁ ያኔ ማስታወቂያ ሚኒስትሩ በእንግሊዞች ነበር የሚመራው።

**ፈለገ ጥበብ** – ትምህርት ሚኒስቴርን ካቋቋሙት አንዱ መሆንዎን ሰምቻለሁ ሁኔታው እንዴት ነበር?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – አየህ ትምህርት ሚኒስቴርን እኮ አምስት ሆነን ነው ያቆየነው፣ እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት እንሠራ ነበር። በአንፃሩ የሰዓት እላፊው አንድ ሰዓት ነበር፣ ምኒስትሩ ነበሩ ማታ ማታ በየቤታችን የሚያደርሱን፣ ያኔ እኔ ጸሐፊ ነበርኩኝ። ሚኒስትራችን መኮንን ደስታ ይባላሉ በኋላ ደጃዝማች ተባሉ። ታድዖ የኔ የአስተማሪ እጥረት ስለ ነበር ራሳቸው ጭምር ፕሮግራም ይዘው ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ያስተምሩ ነበር። የትምህርት ሚኒስቴር ዋና ዴሬክተሩ አቶ ሰረቀም ዳግማዊ ምኒሊክ ያስተምሩ ነበር። ሁላችንም እንደ አንድ ቤተሰብ ነበር የምንተያየው፤ ልንገርዎት! ትምህርት ሚኒስቴርን መጀመሪያ ስናቋቁም ከየቤታችን ወንበርና ጠረጴዛ በመውሰድ (ይዘን በመሄድ) ነው። ይህች ጠረጴዛ (ወደ ጠረጴዛዋ እያመለከቱ) ከኔ ጋር ትምህርት ሚኒስቴር ነበረች፣ ለመታሰቢያ ነው ያስቀመጥኩዋት።

**ፈለገ ጥበብ** – ለመሆኑ በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ ስንት ት/ቤቶች ነበሩ?

**አቶ ዓለመ ሥላሴ** – ምኒልክ ያው የድሮ ነው፣ ተፈሪ መኮንን አለ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (የአሁኑ ኮከበ

www.ethiopianorthodox.org

ጽባሕ) ነበር፤ መድኃኔ ዓለም እንደዚህ እንደዚህ አሉ ብቻ በጣም ጥቂት ናቸው፤ እቴጌ መነንም ነበር።

ፈለገ ጥበብ – በትምህርት ሚኒስቴር ለምን ያህል ጊዜ አገለገሉ?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – ከ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ደርግ ጊዜ ነበርኩኝ፣ በጡረታ የወጣሁት በ፷ ዓመቴ ነው። እንዲያውም በጊዜው የነበረው ሚኒስትር ዶክተር ኃይለ ገብርኤል ዳኘ ተማሪ ሆኖ ያውቀኝ ስለነበር እባክዎን ይቆዩልኝ ብሎኝ ነበር፣ እኔ ግን ይቅርታ አድርግልኝ ብየ ነው የወጣሁት።

ፈለገ ጥበብ – ጡረታ ሲወጡ በምን ኃላፊነት ነበሩ?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – ዋና ዳሬክተር ነበርኩ፣ ብዙውን ጊዜየን ያሳለፍኩት በዋና ጸሐፊነት ነው። የምኒስትሩ ልዩ ጸሐፊም ሁኜ ሠርቻለሁ።

ፈለገ ጥበብ – በዚህ ዓይነት ያን የመሰለ የቅኔ ችሎታዎና ዕውቀትዎ ባይጠቀሙባቸው ነው ያለፉት ማለት ነው?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – (ሳቅ...) ከዛ በፊት ብዙ ጊዜ ተጠቅሜበታለሁ። ኢጣሊያን ሀገራችንን ከለቀቀ በኋላ... ኸረ አሁንም እቀኛለሁ ቅድስት ማርያም፣ ቅድስት ሥላሴ ስሄድ የሚያውቁኝ ሲጋብዙኝ እቀኛለሁ፣ ዛሬ ብቻ የሚያውቁኝ አለቁ... (ፈት ቅጭም) ደግሞ ቅኔ ባደጉና እድሜ በጨመሩ ቁጥር እሱም እያደገ ይሄዳል።

ፈለገ ጥበብ – የቅኔ ነገር ከተነሳ ለመሆኑ ንጉሡና ሌሎች ባለሥልጣናት ፊት የመቀኘት ዕድል አጋጥሞዎት ያውቃል?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – አዎን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ነው የነገሡት። በነገሡ በዓመታቸው የመጀመሪያውን የዘውድ በዓላቸውን ሲያከብሩ ለኔ ተሰጥቶኝ እኔ ነበርኩ የተቀኘሁት። በዛን ጊዜ ቅኔ መቀኘት ከመጠን በላይ ነበር ደስ የሚለኝ።

ፈለገ ጥበብ – ቅኔ በመቀኘትዎ ያገኙት ሽልማትና የማይረሱት አጋጣሚ ይኖራል? በአኳያው ባለሥልጣኖችን ወይም ሌላውን በቅኔ ‹ጐሸም› አድርገው የደረሰብዎት ቅጣት (ተግሳጽ) ካለ ቢነግሩኝ?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – (ሳቅ...) አንድ ጊዜ ሐረርጌ ሳለሁ ጊዜ ያለ ጊዜ (ያለ ሰዓቱ) ተደወለ። አስተማሪየ አለቃ ለማ ይባላሉ፣ እሳቸውን ተከትየ ሄድኩ፣ ብንጠብቅ ብንጠብቅ ሰው የማይመጣ ሆነ። በኋላ አንድ ደብተራ የማነ የሚባል መጣ። ምራ አሉት፣ ተራየ ተወጥቻለሁ ብሎ እጅ ነስቶ ቁጭ አለ። ራሳቸው ተነሱና መሩ፣ እኔን ተመራኝ አሉኝና ተመራሁ። በኋላ ቀስ በቀስ ሰው መጣ ፍትሐሊተ የሚባል ቅኔ አለ፣ ከዛ ተደረሰ። ሲደርስ ያንንም ሲቀኙት ያንንም ሲሉት በመሐሉ ጥቅልል አሉና ተቆጥተው ተቀመጡ። «ዛሬ አዳሬ ጢቆ መወድስ ቅኔ የሚል ጠፍቶ ቁጭ ብለው አነጉት ይባል» ብለው ቁጭ አሉ።

በኋላ አጋፋሪው አጋፋሪ አምሳሉ ይባላሉ መጡና እኔን «እባክህ ሰው ሁሉ ከሥራው ደክሞታልና አንተ ተቀኝ» አሉኝ። እኔም እሺ ተመሪ አምጡና አልኩዋቸው። አመጡ፣ ተቀኘሁ። ጠዋት ሰው ጸጥ ሲል (ቅዳሴ ሲገቡ) አጋፋሪውን «አምሳሉ» ብለው ተጣሩና «ይኸ ልጅ እኮ ዛሬ አገር አውሏል ዕቃ ቤት ውሰደው» አሉ፤ እንድሸለም ነው። ያን ጊዜ የነበረኝ ደስታ እንዲህ አይም ሰልዎት። ደግሞ ያን ዕለት ዜናው በሁሉም ደብር ተሰማ፣ ዛሬ ዓለመ ሥላሴ ዘርፎ ተቀኘ እየተባለ ተወራ።

ፈለገ ጥበብ – የተሸለሙት ምን ነበር?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – አጋፋሪው ይዘውኝ ሄዱና ፲፭ ጥሬ ብር (ማርትሬዛ ብር) ሰጡኝ። እኔም በጣም ደስ ብሎኝ እባክዎ ሌላም ቀን እንደዚህ ላድረግ አልኩዋቸው። (ሳቅ...)። የሽልማት ነገር ከተነሳ ሌላም ልንገርዎ፣ ለንጉሩ ብዙ ጊዜ ነው የተሸለምኩት፣ የአዲስ ዓለም ንብረእድ ነበሩ። ንብረ እድ አድማሱ የሚባሉ፣ ለሳቸው አሰረ ንጉሥ ተቀኘቼ ሰጥቻቸው ሰላሳ ጥሬ ብር ሸልመውኛል። በቅኔየ በጣም ተደንቀው ነበር። ከዚህ ውጭ በቅኔ ምክንያት ከሽልማት በስተቀር የደረሰብኝ ቅጣት የለም።

ፈለገ ጥበብ – አሁን ደግሞ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ልመልስዎ፣ በረዥም ጊዜ የአገልግሎት ዘመንዎ አይረሳኝም የሚሉት የሚያስደስትዎም ሆነ የሚያሳዝን አጋጣሚ ካለዎት ቢያጫውቱኝ?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – አንድ ነገር ልንገርዎት፣ በትምህርት ሚኒስቴር በነበርኩባቸው ዓመታት አንድ ቀንም ከፍቶኝ፣ ቅር ብሎኝ አያውቅም ትዝ አይለኝም። ምክንያቱም እኔ በተፈጥሮየ ከማንም ሰው ጋር በሰላም ነው የምኖረው። አንድ ቀን በአንድ ሰው ጉዳይ ሚኒስትሩ ዘንድ ተጠራሁና ሄድኩኝ። «አይ! ተወው አንተ ለምስክርነት አትሆንም» አሉኝ። እኔም «ምን አጠፋሁ» ብላቸው «ባንተ ዘንድ ሰው ሁሉ እኩል ነው ሰውን አሳልፈህ አትሰጥም» አሉኝ፣ እውነታቸው ነበሩ። አንድ ሰው ከመሥሪያ ቤቱ ተጣልቶ ሲመጣ ወይም ሲሄድ ሌሎች ሲፈሩት እኔ ግን ተከትዬ አባብየ አረጋግቸ ምንብየ ነው የምሰደው። ደግሞ በቢሮየ ብቻ ሁኜ ማዘዝ ሳይሆን በየቢሮው እየሄድኩኝ ችግራችሁ ምንድነው? ምን ብናደርግ ይሻላል? እያልኩ እጠይቃቸዋለሁ። ችግር ካለ አብረን ተመካክረን እንፈታዋለን በቃ...እንደዚህ ነበር ሥራዬን የምሠራው።

www.ethiopianorthodox.org

**ፈ**ለገ ጥበብ – በረዥም የአገል ግሎት ዘመንዎ በርካታ ሚኒስትሮችን አይተዋል (ከሁሉም አብረው ሠርተዋል) ከነዚህ መካከል በሥራው፣ በማስተባበር ችሎታው ይበልጥ የሚያደንቁት ማንን ነው? ምክን ያትዎንም አብረው ቢገልጹልኝ?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – እንግዲህ እውነቱን ልንገርዎት አይደል? ትምህርት ሚኒስቴርን ያቋቋሙት መኮንን ደስታ ናቸው። ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ተግባረ እድ ያቋቋሙት መኮንን ደስታ ናቸው። ያኔ ት/ቤት ባለመኖሩ ጸሐፊ አልነበረም፤ ስለዚህ ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት እስኪሠራ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሦስት ወር በንግድ ሥራ ሥልጠና የሚሰጥ ፕሮግራም ከፈቱ፣ መምህራን ማሠልጠኛ ባለመኖሩ ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ነበር። ይህንን ለጊዜው (ማሠልጠኛ እስከሚሠራ) የሦስት ወር ሥልጠና እዛው ዳግማዊ ሚኒልክ ትምህርት [illegible] ሥልጠናው ወደ መንፈቅ ከፍ አለ። ገሚሱ ሲሰለጥን ገሚሱ ያስተምራል። ብቻ ከዩኒቨርስቲ በስተቀር ሁሉም እሳቸው ያቋቋሙት ጀምረውት የሄዱት ነው። ዩኒቨርስቲንም ያልከ ፈቱት በወቅቱ እዛ ደረጃ የደረሰ ተማሪ ስላልነበረ ነው።

ደጃዝማች መኮንን ምሁር ብቻ ሳይሆኑ ቆራጥም ነበሩ። አንድ ነገር አይሆንም ከተባሉ ለንጉሡ ሥራውን እተወዋለሁ ብለው ነበር የሚጽፉት። ከአቶ መኮንን በኋላ ሥራው ሌላ ሰው አይችለውም በማለት የትምህርት ሚኒስትርነቱን ራሳቸው ንጉሡ ደርበው ይዘውት ነበር። አቶ መኮንን ደስታ በስደት ጊዜ ካይሮ ውስጥ ያስተምሩ ነበር። ከጃንሆይ ጋር አብረው ነው የተመለሱት። ሲመጡ ታዲያ እሳቸው የጐጃም ባላባት ይባላሉ። «መኮንን ደስታ መስፍነ ጊዮን ፀያሔ ፍኖቱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ» እያሉ ወረቀት እየበተኑ ነው የመጡት። አንድ ተጨማሪ ነገር ልንገርዎ ከስደት ሲመለሱ እንግሊዛዊው ጀኔራል ዊንጌት አብሮአቸው ነው የመጣው። ታድያ የኢጣልያ አውሮፕላን ሲመጣ «አንተ ተደበቅ» ይላቸው ነበር «ለምን አንተስ? ሲሉት «እንግሊዝ የእኔ ዓይነት ብዙ ሰው አላት ኢትዮጵያ ግን ያንተ ዓይነት ሰው የላትም ይላቸው ነበር ይባላል። ይህንንም ያጫወቱኝ እሳ ቸው ናቸው።

ለመሆኑ አሁን መሠረተ ትምህ ርት የሚባለው «ምርፋቀ ትምህርት» በሚል ስም የጀመሩት መኮንን ደስታ እንደ ነበሩ ያውቃሉ? ምን ይህ ብቻ ምኞታቸው ትልቅ፣ ሕልማቸው ሩቅ ነበር። ምርፋቀ ትምህርትን ሲጀምሩ በተለይ ዘላኑን (ከብት አርቢውን) ኅብረተሰብ እየዞረ የሚያስተምር ልዩ የትምህርት ቡድን አዘጋጃለሁ ብለው ዕቅድ አውጥተው ነበር። ከቦረና፣ ከሶማሌ በአጠቃላይ ከመላ የኢት ዮጵያ ጠረፍ አካባቢዎች የባላባት ልጆችን በማሰባሰብ በአዳሪነት ማስተማር የጀመሩት እሳቸው ናቸው። በአጠቃላይ የሥራ ሰው ነበሩ። ፐርሶኔል እገሌ ከሥራው ቀርቷል፣ አርፍዶ ይገባል፣ ይቀጣ ሲላቸው «እሱን ተወውና ከሁሉ በፊት የተሰጠውን ሥራ ሠርቷል አልሠራም?» ነበር የሚሉት። ሥራውን ከተወጣ ይሂድ ነበር የሚሉት ሰውን በሰዓት ተቆጣጥሮ ማሠራት አያምኑበትም ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እርስዎስ ምን ዓይነት ሠራተኛ ነበር የሚወዱት?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – እኔም በሰዓቱ የሚገኝ፣ ሥራውን በሚገባ የሚያሸንፍ፣ እወዳለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከቅኔ መምህራን (ሊቃውንት) መካከልስ ማንን ያደንቃሉ? እርስዎን ካስተማርዎት መካከልም ሆነ በዝና ከሚያውቋቸው?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – በቅኔ አለቃ ለማን የሚያህል የለም። በትምህርት ሳይሆን እንደ እድልም ነው፣ ቅኔያቸው ከማንም ከምንም የሚበልጥ ነው። ለብቻ ነው! ደግሞ ሁሉንም ነው የሚያውቁት። መንግሥቱ ለማን ያውቁት ነበር? ከርሳቸው ዘንድ ስማር እርሱ ልጅ ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እንደ ትምህርት ባለሞያነትዎና የረዥም ጊዜ ልምድዎ የአሁኑና የበፊቱን ሥርዓት ትምህርት እንዴት ያዩታል?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – ይህንን መናገር አያስፈልግም!!

**ፈ**ለገ ጥበብ – ለወጣቱ ትውልድ የሚያስተላልፉት የአደራ መልእክት ይኖራል?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – መቼ ይሰማሉ የአሁኖቹ? የዛሬው ልጅ እንደምን አደርክ ቢሉት ምን አገባህ የሚል ነው እኮ? በቅርቡ እዚህ አራት ኪሎ ያጋጠመኝን ልንገርዎ? አንድ ሽማግሌ ምርኩዝ ይዘው ይሄዳሉ፣ ጐብጠዋል፣ አንድ ልጅ በአጠገቡ ሲያልፉ ‹አባት እንዴት ጐበጡ?› አላቸው፤ እሳቸውም «ምን ያደርግ ልሃል አንተ አትደርስበትም» አሉት። አዩ ረገሙት ማለት ነው። እኛ ድሮ ሽማግሌዎች ሲመጡ ከተቀመጥንበት ተነስተን፣ እስኪሄዱ ድረስ ቆመን፣ አሳልፈን...እግዚአብሔር ይባርክህ፣ እደግ እንደዚህ ተብለን ነው ያደግነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ታድያኮ ጥፋቱ የወጣቱ ብቻ ሳይሆን የወላጆችም ነው የሚሉም አሉ። ይህንን እንዴት ያዩታል?



2nd year, Number2, Meskerem 1992

www.ethiopianorthodox.org

አቶ ዓለመ ሥላሴ – ይህም አለ፣ እውነት ነው። እንዲያውም አንዳንድ ወላጆች ተመልሰው ልጆቻቸውን ይፈሯቸዋል። እኔ አያምኑኝም ልጄ እዚህ ዩኒቨርስቲ እያለ እንኳን እቀጣው እቆጣው ነበር። ልጄ ደግሞ ጠባየ መልካም በተማረበት ትምህርት ቤት ሁሉ የተመሰገነ ነበር። ስለዚህ እንዳሉት ካባቶችም ከወላጆችም ጥፋቱ አለ። የትዋልክ? የት ነበርክ? ብለው አይጠይቁም፣ እንዲያውም ለራሳቸው የማያደርጉትን ከአቅማቸው በላይ የሆነውን ነገር ተበድረው ሲያደርጉ ነው የሚታየው፤ የሚያስገርመውም ይህ ነው። ልጅ እኮ ልጅ ነው። መመራት ያለበት በእናትና በአባቱ፣ በቤተሰቦቹ በታላላቆቹ ነው። ስለዚህ በመልካም መንገድ ሊመራ ይገባዋል። እሱም ምክሩን መቀበል አለበት። ግን በታናሽነቱ ካላስተማሩት፣ ካልለመደ ኋላ ምክሩንም አይቀበልም።

ፊለገ ጥበብ – የግብረ ገብ ትምህርት መቅረት ለወጣቱ ትውልድ ጠባይ መበላሸት አስተዋጽኦ አለው የሚሉም ወገኖች አሉ የእርስዎስ አመለካከት እንዴት ነው?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – እንዴ ዋናው ነው እንጂ! ዛሬ ሃይማኖት የት አለ? ማን ሥነ ምግባር ያስተምራል? ማን ይሰብካል? ወጣቱን ትውልድ እኮ ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ? ይህ መጥፎ ነው ወደዚህ ሂድ የሚለው የለም።

ፊለገ ጥበብ – ለመሆኑ የርስዎን ፈለግ የተከተለ ልጅ አለዎት?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – ያለኝ ወንድ ልጅ አንድ ነው፤ እሱም ውጭ ሄዶ እዛ ነው ያለው። እየመጣ ይጠይቀኛል። ሁለቱ ሴቶች ናቸው አንዷ ውጭ ነው ያለችው አንዷ ደግሞ እዚህ እተባበሩት መንግሥታት አዳራሽ (ኢ.ሲ.ኤ) ነው የምትሠራው።

ፊለገ ጥበብ – ከቆሎ ተማሪነት ጋር የተያያዘ ባይሆንም ከተማሪ ጊዜ ትዝታዎ እንደዚሁም በሥራ ላይ ከገጠመዎት ገጠመኞች የሚነግሩኝ አስገራሚ አጋጣሚ ይኖራል?

አቶ ዓለመ ሥላሴ – አንድ የሚያስደንቅ ነገር ልንገርዎት፣ ሐረርጌ አለቃ ለማ ዘንድ ስንማር አንድ ተማሪ እፀፋርስ ጠጣ አሉኝና ሄድኩኝ። እሱ ይለፈልፋል በቃ እንዲህ ነው፣ እንዲህ ነህ እያለ፣ ብቅ ስል «ዓለመ ሥላሴ ዝም ብለህ እኮ ነው ሐዲሳትን የምትደክመው አንተ እኮ ጸሐፊ ሆነህ ነው የምትኖረው» አለኝ። አይገርምም? በወቅቱ እሱ አለኝ ብዬ መማሬን አልተውኩም ተመልሼ ስመጣ ግን እሱ እንዳለው ትምህርት ሚኒስትር ጸሐፊ ሆንኩኝ።

አንድ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ሆነልዎ በጣም አዋቂ፣ ችሎታ ያለው ጸሐፊ ነበረኝ። ለጃንሆይ የሚሄደው ወረቀት እሱ ነው የሚጽፈው፤ ሲበዛ ባለሞያ ነው። ግን ይጠጣል፣ ሲጋራ ያጨሳል። አንድ ቀን (ፕረዚዳንት ቲቶ [illegible] ጊዜ) የቲቶን የሕይወት ታሪክ ተጽፎ በአስቸኳይ ይምጣልኝ አሉ፣ ጃንሆይ። ጸሐፊው ቢፈለግ ቢፈለግ የለም። መኪናየን ያዝኩኝና ደጃች ውቤ ሰፈር ሄድኩኝ። ይገርምዎታል ቁጭ ብሎ ይጠጣል፣ በሥራ ሰዓት እኮ ነው «ምነው እባክህ ሥራውስ?» ስለው «ይልቅስ ለሲጋራ የሚሆን ገንዘብ ካለህ ስጠኝ» አለኝ። ለምኘ አመጣሁትና ጻፈው። ከዛ ሚኒስትሩ ጽሑፉን ሲያዩ ይህ ጸሐፊ ሳይሆን ሰዓሊ ነው ለመሆኑ ደመወዙ ስንት ነው አሉኝ። ደመወዙን ሊጨምሩለት እኮ ነው? ወደቤቱ የሚገባው ደመወዙ በተቀበለ በ15 ቀኑ ነበር። የሚገርመው ጡረታ እንደወጣ የ10ሺህ ብር ሎተሪ ደረሰው ብቻ ታሪኩ ብዙ ነው... አይበቃም?

### አቶ ዓለመ ሥላሴ በተለያዩ ጊዜያት ካበረከቱዋቸው ቅኔያት መካከል

#### መወድስ

ጠቢባን ጸረብት ወወቀርተ እብን፣ ከንቶ ጻመው ለሐኒጸ ምኩራብ ወመርጡል፣
አምጣነ ጻማሆሙ ኮነ ለገጸ ሙስና ወሃጉል።
ባሕቱ ለወልድ ኢያጽአቆ
ሐኒጸ መቅደስ ዘአልቦ አምሳል፣
እንዘ ይሬስዮ ለእብነ ሐቅል
ለሐኒጸ መቅደስ ዘውስጥ ወእንተ አፍአ ዘየአክል፤

#### ለዓለም

አንከሩሂ ሥነ ሕንጺሃ ለዘተበዙረት ድንግል፣
እለ ያስተናድፉ መሠረተ ሐዋርያት ቅድም እስራኤል፣
እስመ በሕንፃ የዐቢ መቅደስ እሙ ለቃል፣
እምሕንፃ ዘተሐንፀ በአርብዓ ወበስምንቱ ቤተ በዓል።

#### ክብር ይእቲ

ተኰርዖተ ርእሱ ለወልድ ሶበ ርእየ ወጥብጣቤሁ ዘባነ፣
ኮከበ ራማ ሕዙን ጸበለ መሬት ተከድነ።
ወአዋልደ ወርህ ሳሌም እመ: ተናጸረ ሥነ፣
ትቤ ፀሐይ ኢትርአያኒ፣ አምጣነ ጸላም አነ!

#### ዕጣነ ሞገር

ተከብቶ ኢትክል ሀገረ ሕማም መጥባሕት፣
መልዕልተ ጊዮርጊስ ደብር እንተ ተሃንጸት፣
አምጣነ እምሩሑቅ ትትራአይ እስከነ አድማስ ሞት።
ቅድመኒ ተሐደሰት፣
በደመ ዘካርያስ ቅብዕ ወበደመ ጳውሎስ ነገሥት
ሕፃናት እስከ አንከርዋ ዘክልኤ ዓመት።

#### አሰረ ንጉሥ

ኃይለሥላሴ እግዚእ አሠርገዋ በቅድመ ብዙኃን ነገሥት፣
ለገነተ ጽጌ ምድርነ ምልዕተ ፍሬ ማኅሌት፣
በሥነ ጽጌያት ጳፆሳት።
ወይእቲከነት ርእሰ ማዕዘንት፣
ዘላዕሌሃ ዮሐቱ ማዕቶት። ✣